ትዮጵያ ህዝብ ከዚህ ያላሰለሰና የማያባራ ግፍ ተንገሽገሸ:: ተሰላቸ::

ኢተፖድህ በተደጋጋሚ እንደገለጸው ይህ አሰልቺነት ደረጃ የደረሰው የወያኔ ግፍ በአገር የመጣ ግፍ ነው:: ይህንን ግፈኛ አገዛዝ ‘ሰለቸን በቃን’ የማለቱ ሃላፊነት የፖለቲካ ፖርቲዎች ሃላፊነት ብቻ ሳይሆን የሲቪክና የሌሎች ስብስቦች፣ ከነሱም አልፎ በጠቅላላው የሃገሪቱ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ሃላፊነት ነው:: በዚች በአንድ ወር እድሜ እንኳን ከፖለቲካ ድርጅቶች በኘሮፌሰር አስራት ወልደየስ፣ ከግለሰብ ዜጎች በእኝህ አዛውንት ታጋይ የቀብር ሥነሥርዓት ላይ የወያኔ ታጣቂዎች በዘፈቀት ተኩስ ህይወቱን ባጡ በወጣት ዓለም አንተ መልሰው ላይ፣ ከሲቪክ ድርጅቶች ደግሞ በነደ/ር ታዩ ወልደሰማያት ላይ የተፈጸሙት ግፎች የወያኔ እብሪት እገሌ ተእገሌ ሳይል በመላ ህብረተሰባችን ላይ የሚቃጣ እብሪት እንደሆነ የሚያመለክቱ ናቸው::

በነዚህ ግፎች መንገሽገሽና በወያኔ እብሪት መሰላቸት ብቻቸውን ሃገራችንን አያድኗትም:: በመንገሽገሽና በመሰላቸት ስሜት ታስረን እስከቀጠልን ድረስ የወያኔ መሪዎች ንቀትና ሌላ ተጨማሪ ግፍ ለመፈጸም የሚያስፈልጋቸው እብሪት እየጨመረ እንደሚሄድ መገንዘብ ይኖርብናል:: ይህንን ሁኔታ ለመቋቋም ኢተፖድህ የሚያቀርበው ጥሪ ‘የሰለቸው ሁሉ ይተጋገዝ’ የሚል አጭርና ግልጽ ጥሪ ነው::

ለእንዲህ ዓይነቱ ትግግዝ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የፖሪሱ ጉባኤ ያመቻቸው ሁኔታና መድረክ አለ:: በዚህም ታሪካዊ መድረክ በመመርኩዝ ኢተፖድህ ቴቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲደባለቁት፣ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ያሉ የሲቪክና ሌሎች ማህበራዊ ስብስቦች በጋራ በሚነድፉት መልክና ደረጃ እንዲተባበሩት፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ደግሞ በድጋፍ ኰሚቴም እየተደራጁም ሆነ በሌላም መልክ እንዲደግፉት [illegible] ያስተላለፈው ጥሪ ከዚህ እንተጋገዝ ከሚል የተለየ ትርጉም የለውም::

የፖሪሱ ጥሪ በወያኔ አገዛዝ ብቻ ሳይሆን በአገር የመጣ ቸግርን በአንድነት በጋራ መቋቋም ሲያቀተን እየተመለከቱ ለተሰላቹና ‘ከእንግዲህ በቃ’ ብለው በአዲስ መንፈስ ትግሉን ለማራመድ ለሚፈልጉ ሁሉ የተላለፈ ሃገራዊ ጥሪ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በሙሉ አወንታዊ መልስ ሊሰጡት ይገባል እንላለን::

ኢተፖድህ ሴክረታር የት
ፍራንክፈርት/ጀርመን